1

## ጎቦ ውቃው - መስከረም 2000

## ለ አንተ "የድህነት ፍልስፍና እና የፍልስፍና ድህነት" ...ቅመም አይሆንም!

የዚህ ጽሁፈ መነሻ፤ የሞተው ጀግናው ወንድሜ ደም ባንተ በትንሹ በተደጋጋሚ ሲላገጠበት በመስማቴ እና በማየቴ ነው፡፡ ... እንቶኔ ምንም ያህል እውቀትም፤ ችሎታም እንደሌለው፤ (የገደል ማሚቶነቱን)፤ እኔ ና እሱ በደምብ ስለምንተዋወቅ፤ ደካማነቱን ቢያንስ እንኩዋን ለኔ እንደማይክደኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ነገር ግን ይህ የእለት እና የወር ገቢውን መሸፈኛውን የሚያገኝበት፤ የሆድ ግዴታው እንደሚያውተረትረው፤ አውቆትም ይሁን ሳያውቀው የተሰጠው የጥፋት ስልጠና ግድ ብሎት የሚያደርገው የመወራጨት አባዜ ሆነና ወዴት እንደሚረግጥም፤ እየረገጠም እንደሆነ አያውቀውም፡፡

ከአቅሙ እና እውቀቱ በላይ እንደሚያንጠራራውም ግልፅ ነው፤ ከዚህም በላይ ወራጅ ዉሃም ሆነ ፍሳሽ ለማሰተላላፍ እንደተጋደመ (ቧንቧ) ከመሆን በላይ ተግባር ስለሌው የእጀራዉን አባቶች የማስደሰት ሙከራው አልሞላ እያለው፡ከመስመር እያለፈበት ነው፡፡ የእሱ አይነቱ አጉራ ዘለልነት፤ አልገባውም እንጂ፤ ምክትል አለቆቹ እነኛ "አዱ ገነት" ላይ የተሰበሰቡት ከአሥራ በላይ የማያልፉት "የአድዋ ወንበዴዎች" እንኳን፤ መሰሪነቱን አንገታቸው ላይ፤ ከጫካም እንደ እንጀራ እናት ጡጦ ታሰሮላቸው ያደጉበት፤በደማቸው የገባውም፤ የግፍ ቁንጮዎቹም፤ የሚራመዱበት መንገድ መድረሻዉን (አደጋዉን) መገመት ስለሚችሉ፤ ከብዙሃኑ ያገሬ ህዝብ የሚያጣላቸዉን፤ ሊያጣላቸው የሚችለዉን፤ጠንቅቀው ስለሚያወቁ፤ ያንተን ያህል አይዳፈሩም፤ ሲፈልጉ ባንተ እና ቢጤዎችህ ይጠቀሙአል እንጂ፤በልጆቹ ደም ቢያላገጡ "አሁንስ ባይኔ መጣህ !" አንደሚያሰኝ፤የሚመጣዉን አደጋ ይገምቱአል፤ እንደተዳፈነ እሳት ቢቆሰቁሱት ሊነሳ የሚችለዉን ምድር አንቀጥቀጥ ሃይል ለሚያወቁት፤ ከገቡበት ግንቦት 1983 ጀምሮ ጥንቃቄአቸው "ልዩ ነው"፤ ይህንንም እነሱ ቢቻ ሳይሆኑ አብረዋቸው አዱ-ገነት የዘለቁትም ሆዳቸዉ የከበዳቸዉ፤ "ተማርን ባዮቹ ታርጋቸዉ ፎረም 84" ተቢዩዎች የግዜ መግፊያ፤ ያዞ እንባ እንዳላዘልቃቸው ውዲያው ነው ያወቁት፡፡

ከምስራቁ-ዓለም በተጨነ ጥይት፤ በቅጥረኛ ነፍሰ-ገዳዮች፤ አብዮት ጠባቂዎች ባደባባይ በግፈኛዉ ግራዚያኒ መንግሰቱ ጥይተ ለሞቱት ለእነኚያ ለእኔ ወንድሞች፤ እህቶች ጀግኖቹ ፤ወያኔም "የ ሰማእታት ሀውለት ላቆም ነው! ፤ አጥንታቸው ተለቅሞ ይዉጣ!፤ ብሎ የነበረው "ያንድ ሰሞን የቴሌቪዥን ትር|ት" ፤ የዓፄው ቤተ መንግስት መግቢያ "ሬድ-ካርፔት" አድርገውት የነበረው ተውኔት የቅርብ ግዜ ትዝታ ነው፤ ምነው?! የሚለው የህዝብ ድምፅ ሲሰማ፤ ነገሩ ሲጣድ እና ሲፈላ፤ ለማርገቢያው "የመስረት- ድንጋይ ይጣል!" ፤ "የ ዲዛይን ውድድር ይደረግ!"፤ አደጋው ያላቸውን ፍራቻ ያሳይሃል፤ ዳሩማ ወያኔማ ወያኔ ነው፤ ይህቺ ያድዋ ጮሌነትማ (ሊፕ-ሰርቪስ) መሆኑአን "ወጡ ሳይወጠወጥ.." እንደሆነ ጠንቅቀን እናወቃለን፡፡ እነኚያ ንፁሃን እልፍ ወጣቶች ደም ክብር በላይ፤ ለአድዋዎቹ ወንበዴዎች ንግስና፤ ለኤርትራ ግንጠላ ባለዉለታዋ "አአ ህህ ያያ ! !" መታሰቢያ ቆሞ የለ፤ "እሱን ጢሲ ...." አለ የአገሬ ኦሮሞ፤ በእነኚህ የአድዋ ወንበዴዎች የግፍ ዘመን፤ ገና ከጅምሩ በጠራራ ፀሐይ በራፉ ላይ ከተደፋው አሰፋ ማሩ እና በምርጫ 97 ማእግስት ከምእራቡ አለም በተጫነ ጥይት እና ስልጡን አነጣጥሮ ተኩአሽ ግንባሩን የተመታው ሙሽራው ያጎቴ ልጅ "ተስፋዬ"...፤ ሽብሬ ደሳለኝ...፤ የፈሰሰው

ደማቸው አሁንም ትኩስ ነው፤ በጠቅላላው ቤተሰቡ ላይ ለደረሰው ሐዘን እና የህመሙ መጠን ከእኛ በላይ የሚያምው የሚኖር አይምስለኝም።

በሚቹ በየጀግናው ኢሕአፓው ወንድሜ ምክኒያት በተለይ እናቴ እና በአጋዚ ጦር በተገደለው ተስፋዬ ሞት የአጎቴ ሚስት ከደንቡ በላይ ይኸው እስከ አሁን ማቅ እንደለበሰች፤ ምላው ወገንም በከባድ ሐዘን ላይ ነው። አንተ ግን ይኸው እስከ አሁንም ድረስ ከማንም ከሐዲ እና ጠላት በላይ ያልሞከሩትን ጭፍን ሙከራ እየሞከርክ በመሆኑ "ማሙሽ እሱ እፉ ነው!" እያልን ልንነግርህ ባልተገባ ነበር።
የዛሬዉ የኛ ልሳን ፤ የኛ ነፃ አዉጪ፤ በደርጉ ዘመንማ ምን ሆነህ? ምን እንደሰራህ? እንተዋወቅ የለ፤ ያሁነኛዉን ምድብህን (ሴል ሜምበርነትህ)፤ በአድዋዎቹ ጮሌዎች ስልት፤ "ባገር ክደት ክስ ሽፋን ስም" የለበስከው ማሊያ አሰላለፍህን የደበቀልህ የሚመስልህ ደካማ ብትሆንም፤ በእኔ ሚዛን ያንተ "ትንሽነት" (ቀላልነት) ፤ ጉዳቱ ጊዜያዊ ነው የሚል እምነት ቢኖረኝም በዚያ ባንተ ትንሽነት መጠን (ልክ) የሚገኙትን ተላላ ወንድሞቼን ላንድ ቀን ግራ ማጋባት የለብህም የሚል ፅኑ እምነት አለኝ።

ዛሬ ግን እውቀት እንኩአን የለህም! "የዘሬ ያንዘርዝረኝ!" ሆነ እና ዋና ዋናዎቹ ደሞዝ ከፋዮችህ ያልደፈሩትን፤ እና ያላለፉትን መስመር በማለፍህ፤ አንተም ታውቀዋለህ፤ ይህ ድርጊትህ ፊንጠዚያዉ፤ ለAድዋ ወንበዴዎች፤ ቅጥረኞቻቸው ሆዳሞች፤ ለባዶዎቹ አብዮት ጠባቂዎች፤ የአብዮት ጠባቂ ልጆች፤ብቻ ናቸው እንደ "...-ጀበና" የሚፈሉት፤ "ሰርጓ እንዳማረላት ሙሽራ" እነኚህም ካንገት በላይ ሊፈነድቁብን፤ ትከሻቸዉን ሊሰብቁብን አንፈቅድም፤ የአንተም ሆነ የእነሱ "ፈንደቂያ" ከልብ ሳይሆን፤ በአንተ ዙሪያ የሰበሰባቸዉም፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየኮረኮረ አረፍት፤ ጤና የነሳቸው፤ የሰማእታቱ፤ የጀግኖቹ፤ የኢሕአፓ አባላቱ፤ የሙሽሮቹ ወንድሞቼ እህቶቼ ደም ነው ከትክክለኛ ፍትህ መደበቂያ ዳስ የጣልክላቸዉ መስሎአቸዉ ጮቤ የዳዳቸው፤ ይህንንም ከቶ አንፍቅድም።

የእኔ አይነቶቹ እልፍ ናቸው፤ በደርግ ጥይት መሃል መርካቶ በተገደለው በሙሺራው ወንድሜ ሞት እንዲሁም በአጋዚ ጥይት መሀል ግንባሩን ተመቶ በሞተው በሙሽራው ያክስቴ ልጅ ደም ማላገጡን ቤተሰባቺን በሞላ ለደቂቃ በቀልድ አናየዉም ።

አይ ድፍረትህ! ሌላው ከማስገረምም የሚያስቀው የሰሞኑ ድራማህ፤እንደ አምናው የምርጫ ሰሞን "ተግባር- ሊግ" ወጣቶች ያስገደልክበት እቃ፤ እቃ ጫዋታ ሰሞኑን የሰባ-ሚሊዮን ሕዝብ ምርጫ እና ወደር የሌለዉን ጀግና የኢትዮጵያ ልጅ በኢንጅነር ሀይሉ ሻውል የዋሺንግተን-ዲሲ አቀባበል ስነ-ስርአት ላይ፤ ሲሉ ሰምተህ የለ፤ እነኚሁኑ አብዮት ጠባቂዎችን እፍኝ ከማይሞሉ ልጆቻቸው ጋር በትንሽ ቡድን አደራጅተህ በገማ እንቁላል ለማስመታት መንጠራራትህ አጀብ ነው። ተሰፍሮ የሚሰጠህ ምስህ ለምትቀባጥረው የሚመጠን አልመስል እያለህ የምታረገው መቅነዝነዝ "መስመሩን አለፈ !" ለዲስኩርህ እና ለድረ- ገፅህ መሙያ እራስህን ችለህ ለመቆም የእውቀትና የሐቅ ድሕነት በአቅምሕ ከምትሽከመው በላይ በመሆኑ እነዚያው ቀጣሪዎችህ ጋ ፤ ኮንትራቱን እንዲያቀሉልህ፤ የውሸትዋን "ያገር ክደት ክስ" እንዲያነሱልህ ተማጠን) ።

ኤልያስ ላንተ "የድሕነት ፍልስፍና እና የፍልስፍና ድሕነት ኢሕአፓ ቅመም አይሆንም"

ይህ መልእክት ለአንተ ብቻ ሳይሆን አባሪዎቺህ እና ቢጤዎቺህን ይመለከታል።